# ሰርጉ ነው አበሻ

ባይሞትም ሙት ነበር ፣ ቁም እስር የገባ
በራሱ ጥላ እንኳን ፣ ሆዱ የሚባባ
ለ 21 ዓመት ፣ ዙሪያውን ግንብ አጥሮ
ድመት እንዳየ አይጥ ፣ ሲደነግጥ ኖሮ
በቁሙም ሙት ነበር ፣ ሁሌ ተሰውሮ
ተገላገለ እንጂ ፣ ከፍርሃት ኑሮ ።

የማይሰለቻቸው ፣ በጣቃው ፣ በጣቃው ፣ የሚተረተሩ
በደደቢት ድግምት ፣ ፊጥኝ የታሰሩ
ደነዝ ወያኔዎች ፣ ጭፍን የታወሩ
ሲኦል በወረደ ፣ በሁለተኛ ወሩ
ዛሬ ሞተ ይሉናል ፣ ቋንጣውን ሊቀብሩ ።

አሁን የሰው ፣ ደረቅ እያገላበጡ
ትኩስ ሆነ ቋንጣ ፣ ለውጥ ላያመጡ
ዛሬ ሞተ ማለት ፣ አርባ እንዳያወጡ
አበሻ ግድ የለው ፣ መካሪ ባላጡ ።

ሰልስት የለው አርባ ፣ ፍታትም አይሻ
ቢሻቸው ያቃጥሉት ፣ ይጣሉት ለውሻ
መልካም ለወያኔ ፣ መስማትም አንሻ
እነሱ ያልቅሱለት ፣ ሰርጉ ነው አበሻ ።

እንኳንም ሄደለን ፣ የተሰናበተ
ግና ምን ያደርጋል ፣ ስርአቱ ካልሞተ
ወያኔውን ቀብሮ ፣ ወያኔው ከመጣ
እውነት አልበረደም ፣ ዛሬም ያምላክ ቁጣ ።

ፋሽስት ሞተ ብዬ ፣ ሃዘን አይገባኝም
ባንድ አጋሰስ መሞት ፣ ምንም አልሞኝም
አጋሰሱ ሞቶ ፣ አጋሰስ ላይተካ
ዋስትና ሳይኖረኝ ፣ የምን ሆያሆዬ ፣ ምንድነው ፋሲካ?

ይሄ ያገር ሰንኮፍ ፣ ከሄደ ተነቅሎ
መሰሉን ሳይተካ ፣ ቶሎ ፈጠን ብሎ
እንደ ደነገጡ ፣ እንደ ተሸበሩ
አይናችን የሚሉት ፣ ጠፍቶ እንደታወሩ
ግራ እንደገባቸው ፣ ሳይጠናከሩ
ባራቱም ማዕዘን ፣ ተዘጋግቶ በሩ
ሁሉም ባካባቢው ፣ ያንድድ ፣ እሳቱ ጫሩ
እንዳለ ወያኔ ፣ ይግባ መቃብሩ ።

ተጓተው ሲሄዱ ፣ ሁሉም በየተራ
ስርአቱ ሲቀበር ፣ ከመለሰ ጋራ
ለነሱ ሲጨልም ፣ ለጭቁን ሲበራ
ጎጠኞች ቤት ለቅሶ ፣ ለህዝቡ ዳንኪራ
ያኔ ነው ፋሲካ ፣ እልልታ ጭፈራ ።

ታዛቢው ...August 21, 2012